

ለማምለጥ በዱር አእዋፍ ፍልሰት የተጠቀመ ይመስለኛል።

አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ

# ታዳጊው ልዑል

ከደራሲው ውኃ ቀለም ሥዕሎች ጋር

ተርጓሚ ዶ/ር ብርሃኑ አበበ

ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ
የመ.ሳ.ቁ. 57
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በጽሑፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የሥነ ጽሑፍና ኪነጥበብ ሥራዎች ባለቤትነትን በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስከ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ አንኳን መልሶ ማሳተም፣ መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።

የመጀመሪያ ኅትመት 2002 ዓ.ም

© ዶ/ር ብርሃኑ አበበ፣ 2002 ዓ.ም

ISBN: 978-99944-0-019-5

የተባበሩት አታሚዎች ኃ. የተ. የግ. ማ.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## የተርጓሚው መቅድም

### ታዳጊው ልዑል

አንቷን ሰንት- ኤግዙፔሪ ፈረንሣዊው ኤሮፕላን አብራሪና ደራሲ ይህን ታሪክ የጻፈው በ1943 እ.ኤ.አ ነው:: አብራሪው የሞተር ብልሽት ይደርስበትና ኤሮፕላኑን ሰሐራ በረሃ ውስጥ ሲያሳርፍ፣ እዚያ ብቸኝነትን ተዝናንቶ የተቀበለ የሚመስል አንድ ወጣት ያገኛል:: ልጁ አንድ ሕዋ አካል ላይ ከአንዲት ጽጌሬዳ ጋር ብቻቸውን ሲኖሩ የጓደኛው ቀብራራነት አስመርሮት አገር ጥሎ የጠፋ ነው:: በመሬት ሲጓዝ እግረ መንገዱን ካጋጠሙት የተለያዩ ሰዎች መካከል ንጉሥ፣ የገጸ ምድር ተመራማሪና የጉዳና መብራት አብሪ ሳይቀር ቢገጥሙትም፣ ሁሉም በየበኩላቸው የሚጨነቁት በማይረባ ነገር መሆኑን ይደርስበታል:: ሰሐራ ውስጥ ከሚኖር ፌኔክ ከተባለ ድንክ ቀበሮ ጋር ያካሄደው ውይይት ግን የፍቅርን ትርጉም አስገነዘበውና ጽጌሬዳይቱ ትናፍቀው ጀመር:: በዚህም ምክንያት ወደ ነበረበት ዓለም ተመልሶ ለመሄድ አንድ እባብ እዲነድፈው አደረገ:: ተነባቢነቱ ለሕፃናት እንኳ ምንም ችግር የሌለበት ይህ ደስ የሚል ቅኔ ለበስ ትረካ፣ ያዘላቸው ምስጢራውያን ተምሳሌቶች እንኳን ታዳጊውን አንጋፋውን አንባቢ ሳይቀር በሐሳብ የመመሰጥ ጠባይ ይታይባቸዋል::

ዶ/ር ብርሃኑ አበበ

## አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ


ፈረንሳዊው ኤሮፕላን አብራሪና ደራሲ አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ ሊዮን ከተማ ሰኔ 29 በ1900 እ.ኤ.አ ተወልዶ በ1944 በኤሮፕላን ተልእኮ ለመፈጸም ወጥቶ የደረሰበት እስከ ዛሬ ሳይታወቅ እንደ ጠፋ የቀረ ታላቅ የብዕር ሰው ነው።

የባሕር ኃይል ትምህርት ቤት መግቢያ ውድድሩን ሲጨርስ፣ ብሔራዊ አገልግሎቱን በአየር ኃይል ውስጥ አጠናቅቆ የንግድ መሥመር ተቀጣሪ ሆኖ ነበር። ብዙም ሳይቆይ በሙከራ ኤሮፕላኖች አብራሪነት ፓሪስ፣ ሳይጎን፣ ኒውዮርክና ቴርደፌ አዲስ በረራዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳካ ሁኔታ ፈጸመ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በ1940 በአየር አሰሳ ተመድቦ ከሠራ በኋላ ወደ አሜሪካ ሄዶ ነበር። በ1942 እንደገና ወደ ሰሜን አፍሪካ ተመልሶ ትግሉን ቀጠለ። የአየር ተልእኮ ለመፈጸም ስኮርስ ተነሥቶ እንደ ወጣ የቀረው ሐምሌ 31 ቀን 1944 ነው። አንቷን ድሰንት- ኤግዙፔሪ ከአብራሪነቱ ጐን ለጐን ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካተረፉለት ብዙ መጻሕፍት ውስጥ «የደቡብ መልእክተኛ» «የሌሊት በረራ» «የሰዎች መሬት» «የጦር አየር አብራሪ» የተሰኙትን መጥቀስ የደራሲነቱን አድማስ ለማመልከት ይበቃል። ከሁሉም የበለጠ ተቀባይነት ያገኘው ግን በ1943 የደራሲው የመጨረሻ መጽሐፉ «ታዳጊው ልዑል» ነው። ይህ ታሪክ በየቋንቋው ተተርጉሞ ከዓለም የሥነ ጽሑፍ አንጋፋ ውጤቶች መካከል የክብር ቦታውን ይዞ በምስጢራዊ ውበቱ አንባብያንን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሲማርክ ይኖራል።

## ለሌዎን ቨርት

ይህን መጽሐፍ ለአዋቂ ስላበረከትኩት ሕፃናትን ይቅርታ እጠይቃለሁ። በቂ ምክንያት አለኝ። ይህ ትልቅ ሰው በምድር ዓለም ከማንም የሚበልጥብኝ ወዳጄ ነው። ሌላው ምክንያቴ ይህ አዋቂ ግለሰብ የሕፃናትን መጽሐፍ ጨምሮ ማናቸውንም ነገር የመገንዘብ ችሎታ ስላለው ነው። ሦስተኛው ምክንያት ይህ አዋቂ ሰው ተርቦና ታርዞ ፈረንሣይ አገር ነዋሪ በመሆኑ በሚገባ መጽናናት ያሻዋል። ይኸ ሁሉ ምክንያት የማይበቃ ከሆነ አዋቂው ግለሰብ ዱሮ ሕፃን በነበረበት ወቅት ይህን መጽሐፍ ለማበርከት ፈቃደኛ ነኝ። አዋቂ ግለሰቦች ሁሉ በጊዜአቸው ሕፃናት ነበሩ የሚያስታውሱት ግን በመጠኑ ናቸው። ስለዚህ አቀራረቤን ላርም።


ለሌዎን ቨርት
ታዳጊ በነበረበት ወቅት



ድሮ ስድስት ዓመት ሲሆነኝ እውነተኛ ታሪኮች በተሰኘ ርእስ ስለ ድንግል ደኖች በተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ግሩም ሥዕል አየሁ:: ዘንዶው አንድ የዱር አውሬ ሲውጥ ነው:: የሥዕሉ ግልባጭ ይኸው::


«ዘንዶዎች ሰለባቸውን እንዳለ፣ ሳያኝኩ ይውጣሉ፣ ከዚያም መንቀሳቀስ ይሳናቸውና የበሉትን ሲያዋሕዱ ስድስት ወር ይተኛሉ» ይላል መጽሐፉ::

እኔም ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ውስጥ ስለሚካሄደው ነገር ሁሉ ብዙ ካሰላሰልኩ በኋላ ተራዬን በቀለም እርሳስ የመጀመሪያውን ሥዕል ነደፍኩ:: ቊጥር አንድ ሥዕሌን ማለት ነው:: ይኸንን ይመስላል፣



ሥዕሌን ለአዋቂ ሰዎች አሳየሁና ያስፈራቸው እንደሆነ ጠየቅኋቸው::

እነሱም፣ «ባርኔጣ ምኑ ያስፈራል?» ብለው መለሱልኝ። የኔ ሥዕል የሚያሳየው ባርኔጣ ሳይሆን ዘንዶ ዝሆን ውጦ ሲያዋሕድ ነው። ከዚያ አዋቂዎቹ እንዲገባቸው የዘንዶውን ሆድዕቃ ሣልኩላቸው፤ ሁልጊዜ ማብራሪያ ይፈልጋሉ። ሁለተኛው ሥዕሌ ይኸንን ይመስላል፣



አዋቂዎች ክፍት ዘንዶና ድፍን ዘንዶ የምለውን ምሳሌዬን ትቼ ይልቅ ወደ መልክዓ ምድር፣ ወደ ታሪክ፣ ሒሳብና ወደ ሰዋስው እንዳተኵር መከሩኝ። ዕጹብ ድንቅ የሆነውን የሠዓሊነት ሙያ በስድስት ዓመቴ እርግፍ አድርጌ የተውኩት በዚህ ዓይነት ነው። ቍጥር አንድና ቍጥር ሁለት ሥዕሎቼ ተቀባይነት ባለማግኘታቸው ተስፋ ቈርጬ ነው። አዋቂዎቹ ሁልጊዜ አንድ ነገር ካላስረዷቸው አውቀው አይገባቸውም፤ አሁንም አሁንም ማስረዳቱ ደግሞ ልጆችን ያክል።

ከዚያም ሌላ ሙያ ለመምረጥ ተገድጄ ኤሮፕላን ማብረር ተማርኩ። ዓለም ላይ በያለበት በኤሮፕላን ሄጃለሁ። የገጸ ምድር ዕውቀት እውነትም ብዙ ጠቀመኝ። ቻይናን ከአሪዞና ወዲያው ለይቼ ለማወቅ ቻልኩ። ለሊት መንገድ ሲጠፉ በጣም ይጠቅማል። በሕይወቴ ከአያሌ ቁምነገረኛ ሰዎች ጋር ብዙ ጊዜ ለመገናኘት የቻልኩት በዚህ ሁኔታ ነው። አዋቂ ሰዎች ቤት ብዙ ጊዜ ኖሬያለሁ። ከቅርብ አስተውያቸው ነበር። ያም ሆኖ አስተያየቴን እምብዛም አላሻሻለውም።

በመጠኑም ቢሆን አስተዋይ የሚመስለኝ ሰው ሲያጋጥመኝ ባስቀመጥኩት ቍጥር 1 ሥዕሌ እፈትነው ነበር። እርግጥ የሰው ነገር የሚገባው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። መልሱ ግን

ሁልጊዜም «ባርኔጣ ነው» የሚል ነው። በዚህ ጊዜ ስለ ዘንዶም፣ ስለ ድንግል ደንም፣ ስለ ከዋክብት አሳነሣበትም። እሱኑ መስዬ እቀርበዋለሁ። ስለ ካርታ ጨዋታ፣ ስለ ጎልፍ፣ ስለ ፖለቲካና ስለ ክራቫቶች አወራለታለሁ። አዋቂውም ሰው እንደኔ ያለ ልባም ግለሰብ በማግኘቱ ይደሰታል።

## ፪

የዛሬ ስድስት ዓመት ሰሐራ በረሃ ውስጥ እክል እስካጋጠመኝ ድረስ የልቤን የማነጋግረው ሰው ሳይኖረኝ በብቸኝነት እኖር ነበር። እሞተሩ ውስጥ አንድ ነገር ተሠበረ። ሜካኒክ ሠራተኛና አብረውኝም የሚጓዙ ሰዎች ስላልነበሩ አስቸጋሪውን ጥገና ብቻዬን ለመወጣት ተዘጋጀሁ። የሞት ሽረት ጉዳይ ነበር። የነበረኝ የመጠጥ ውኃ ክምችት ቢበዛ ለሳምንት ብቻ የሚበቃ ነበር።

የመጀመሪያውን ሌሊት ሰው ከሚኖርበት አንድ ሺህ ማይል በሚርቅ አሸዋ ላይ አደርኩ። መርከቡ ሰምጦበት ውቅያኖስ መካከል በታንኳ ከሚንሳፈፍ ሰው የባሰ ብቸኛ ነበርኩ። ሲነጋጋ ያልተለመደ ሰላላ ድምፅ ከእንቅልፌ ሲያስነሳኝ የደነገጥኩት ድንጋጤ ይታያችሁ። ድምፁ

- እባክህ... በግ ሣልልኝ ይላል።
- ምን አልክ?
- በግ ሣልልኝ ...።

መብረቅ እንደ መታው ሰው እመር ብዬ ቆምኩ። ዓይኖቼን አባበስኩ። ተጠንቅቄ አየሁ። አንድ በጣም ልዩ የሆነ ትንሽዬ ልጅ በጽሞና ይመለከተኛል። ከጊዜ በኋላ ልሥለው የቻልኩት መልኩ ይኸውና የኔ ንድፍ ግን በእርግጥ የሱን ወዘና አይደርስበትም። የኔ ጥፋት አይደለም። ስድስት ዓመት ሲሆነኝ

አዋቂዎቹ የሠዓሊነት ሙያዬን አጨናግፈውብኝ ከድፍን ዘንዶና ከከፍት ዘንዶ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር መሣል አልተማርኩም:: የተከሠተውን ልጅ በአድናቆት ፍጥጥ ብዬ አየው ጀመር:: ሰው ካለበት አካባቢ አንድ ሺህ ማይል ርቀት ላይ እንደ ነበርኩ አይዘንጉ:: ልጁ ደግሞ ያለበት ቦታ የጠፋው፣ በረሃብ ለሞት የተቃረበ፣ ውኃ ጥም የገደለው፣ በፍርሐት የተሸበረ አይመስልም:: እበረሃ መካከል ከሰው መኖርያ አንድ ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ የጠፋ ልጅ በጭራሽ አይመስልም::

ቆይቼ ቆይቼ መነጋገር ስችል፣

- ለነገሩ: ... እዚህ ምን ልታደርግ መጣህ አልኩት::

- እሱም መልሶ በለስላሳ ድምፅ እንደ ትልቅ ቁም ነገር፣


- እባክህ ... የበግ ሥዕል ሣልልኝ አለኝ::

ምስጢሩ ከመጠን በላይ ከባድ ሲሆን ደፍሮ እምቢ አይባልም:: ሰው ከሚኖርበት አካባቢ አንድ ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ ለሞት አደጋ በተጋለጥኩበት ሁኔታ አድራጎቴ ትርጕም የሌለው ቢመስለኝም ከኪሴ ወረቀትና የቀለም ብርዕ አወጣሁ:: እዚህ ላይ ግን እኔ በመሠረቱ የተማርኩት ገጸ ምድር፣ ሒሳብና ሰዋሰው መሆኑ ትዝ አለኝና ልጁን (እንደ መበሳጨት እያለኝ) ሥዕል መሣል አላውቅበትም አልኩት:: እሱ ግን መልሶ፣

- ግድ የለም:: የበግ ሥዕል ሣልልኝ::

የበግ ሥዕል ሥዬ ስለማላውቅ ከምችላቸው ሁለት ሥዕሎች አንዱን ሣልኩለት:: የድፍኑን ዘንዶ::

- የለም! የለም! ዘንዶ ሆድ ውስጥ ያለ ዝሆን አልፈልግም:: ብሎ ልጁ ሲመልስልኝ ጊዜ በጣም ደነቀኝ:: ዘንዶ አደገኛ ነው፤ ዝሆንም ቦታ ያጣብባል:: እኔ ቤቴ ጠባብ ነው: የምፈልገው በግ ነው:: የበግ ሥዕል ሣልልኝ:: ከዚያ ሣልኩለት:: ትክ ብሎ አየና፣



- አይሆንም ! ይኸ በሽታ አጥቅቶታል
- ሌላ ሣልልኝ።




ሣልኩ።
ወዳጄ ከደገኛ ፈገግታ ጋር በጸጋ ተቀብሎ፣
- እየው ... ይኸኮ በግ አይደለም
ወጠጤ ነው። ቀንድ አለው።
ሥዕሌን መልሼ ሣልኩ፡
አሁንም እንደ ፊተኞቹ ሁሉ ተቀባይነት
ሳያገኝ ቀረ።



- ይኸኛው አርጅቷል። እኔ እምፈልገው
ብዙ ዓመት የሚኖር ነው። ታዲያ ትእግሥት
አጣሁና ሞተሬን መፍታት ለመጀመር ቸኩዬ
ነበርና ይኸንን ሥዕል ጫር ጫር አደረግሁ። እናም
- ይኸ ሣጥኑ ነው። እውስጡ የምትፈልገው
በግ አለ ብዬ ጣል አደረግሁለት።



ግን ወጣቱ ዳኛዬ ፊቱ ወገግ ሲል
አየሁና በጣም ገረመኝ።
- ልክ እንደዚህ ነው የምፈልገው!
ለበጉ ብዙ ሣር የሚያስፈልግ ይመስልሃል?
- ለምን?
- ቤቴ ጠባብ ስለሆነ ነዋ ...
- ሳይበቃው አይቀርም። የሰጠሁህ በግ አነስተኛ ነው።
ወደ ሥዕሉ ጐንበስ አለና፣



- ይህን ያህል ትንሽ አይደለም ... ዓየኸው! እንቅልፍ ይዞታል ...።

ከታዳጊው ልዑል ጋር የተዋወቅነው በዚህ ዓይነት ነው።

## ፫

ከየት እንደ መጣ ለማወቅ ብዙ ጊዜ ፈጀብኝ። ብዙ ጥያቄ የሚያቀርብልኝ ታዳጊ ልዑል የኔን ጥያቄዎች ፈጽሞ የሚያዳምጥ አይመስልም ነበር። እንደ ዘበት የሚወረውራቸው አንዳንድ ቃላት ናቸው ቀስ እያሉ ሁሉንም እንዳውቀው የረዱኝ። ለምሳሌ ኤሮፕላኔን መጀመሪያ ሲያይ (አሳሳሉ በጣም ስለሚያስቸግረኝ ኤሮፕላኔን አልሥለውም) እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ፡

- ያ ነገር ምንድነው?

- ያ ነገር ዕቃ አይደለም። ይበራል። ኤሮፕላን ነው። የኔ ኤሮፕላን ነው።

እናም መብረር እንደምችል ስነግረው ኩራት ተሰማኝ።

አሁን ድምፁን ከፍ አድርጎ፡

- እንዴት! ከሰማይ ነው የወደቅኸው!

- አዎ አልኩ በትሕትና።

- ወይኔ! ይገርማል...።

ታዳጊው ልዑል ደስ የሚል ሣቅ ከት ብሎ ሲሥቅ በጣም ተበሳጨሁ። የደረሰብኝን መከራ በቁም ነገር እንዲያይልኝ እፈልጋለሁ። ከዚያም ቀበል አድርጎ፣



- እንግዲያው አንተም ከሰማይ ነዋ የወረድኸው? ከየትኛው የሕዋ አካል ነው?

እዚህ የመገኘቱ ምስጢር ወዲያው ውልብ አለብኝና ሳይጠብቀው፣

- እንግዲያው አንተ ከሌላ የሕዋ አካል ነዋ የወረድከው?

ብዬ ጠየቅሁት ግን መልስ አልሰጠኝም። ኤሮፕላኔን እየተመለከተ በቀስታ ራሱን በመነቅነቅ የአዎንታ ምልክት አሳየኝና፣

- እርግጥ እዚህ ውስጥ ሆነህ ከሩቅ መምጣት አትችልም...። እናም በሐሳብ ተውጦ ብዙ ቆየ። ከዚያም የኔን በግ ከኪሱ አወጣና ሀብቱን በተመስጦ ያስተውል ጀመረ።

«ሌሎች የሕዋ አካላት» በማለት የምስጢሩን ጫፍ ሲገልጥልኝ ምን ያህል እንደ ከነከነኝ ይታያችኋል። ጠለቅ ብዬ ለማወቅ በመሞከር፣

- ማሙዬ ከየት ነው የመጣኸው? አገርህ የት ነው? በጌን የት ልትወስደው ነው?

በዝምታ አሰላሰለና፣

- የሰጠኸኝ ሣጥን ጥሩነቱ ማደሪያ ቤት ይሆነዋል አለኝ።

- ነው እንጂ። ጥሩ ልጅ ከሆንክ ቀን ቀን ለማሠር የምትገለገልበት ገመድ እሰጥሃለሁ። ችካልም።

የቀረበለት ሐሳብ ታዳጊውን ልዑል የረበሸው ይመስላል።

- ማሠር? ምን ዓይነት አስተሳሰብ ነው!

- ካላሰርከውኮ የትም ሲዞር አንድ ቀን ይጠፋል። ...።

ታዳጊው ልዑል ቢ612 በተባለው የዓውደ ፀሐይ ሕዋ አካል ላይ።

ወዳጄ እንደገና ከት ብሎ ሣቀ።

- የት ይሄዳል ብለህ ነው?

- የትስ ቢሆን። ቀጥ ብሎ ፊትለፊት ቢሄድስ? ...።

እዚህ ላይ ታዳጊው ልዑል በቁም ነገር፣

- ግድ የለም፣ ቤቴ በጣም ጠባብ ነውኮ!



ታዳጊው ልዑል ቢ612 በተባለው የዓውደ
ፀሐይ ሕዋ አካል ላይ::


ከዚያም እንደ መተከዝ ያለው ይመስላል፣
- ፊት ለፊት ተሂዶ የትም አይደረስ አለ።

## ፬


እንግዲህ ሁለተኛ በጣም ትልቅ ነገር ማወቄ ነው። የልጁ የትውልድ ሕዋ አካል ከአንድ ቤት እምብዛም አይሰፋ ማለት ነው! በዚህ ብዙም አልደነቀኝ። እንደ መሬት እንደ ጁፒቴር እንደ ማርስና እንደ ቬኑስ ካሉት ስም ከወጣላቸው ታላላቅ ከዋክብት ውጪ አንዳንድ ጊዜ በጣም ከማነሣቸው የተነሣ በመነጥር ለመየት የሚያስቸግሩ በመቶዎች የሚቈጠሩ ሕዋዎች አሉ። የሥነ ከዋክብት ተመራማሪ አንዱን ሲያገኘው የአኃዝ ስም ያወጣለታል።

ለምሳሌ ትንሽቷን «የሕዋ አካል 325 ይላታል።» ታዳጊው ልዑል ቢ612 ከተባለው ሕዋ አካል ለመምጣቱ አንዳንድ አስተማማኝ ምክንያቶች አሉኝ። ይኸ ሕዋ አካል በመነጽር የታየው አንድ ጊዜ ብቻ እ.ኤ.አ. በ1909 በአንድ ቱርካዊ የከዋክብት ተመራማሪ ነው።

ተመራማሪውም በወቅቱ ለሥነ ከዋክብት ዓለም አቀፍ ጉባዔ ግኝቱን በስፌው አሳውቆ ነበር።








ነገር ግን በሀገረሰብ
ባህላዊ ልብሱ ምክንያት
ማንም አላመነውም ነበር::
አዋቂዎቹ ይኸው ናቸው::
እንደ ዕድል ሆኖ
ለሕዋ አካል ቢ612 ዝና
የበጀው አንድ የቱርክ
አምባገነን ሕዝቡን እንደ ፈረንጅ ካልለበስክ ይሙት በቃ
እፈርድብሃለሁ ብሎ ማስገደዱ ነው:: የሥነ ከዋክብቱ
ተመራማሪ በ1920 እ.ኤ.አ. ዘናጭ ልብስ ለብሶ ማስረጃውን
በድጋሚ ሲያቀርብ ጊዜ ሐሳቡን ሁሉም ተቀበሉት::

የሕዋ አካል ቢ612 ታሪክን በዝርዝር መተረኬና አኃዙንም
መግለጼ በአዋቂዎቹ ሰዎች ምክንያት ነው፡ አዋቂዎቹ አኃዞች
ይወዳሉ:: ስለ አዲስ ወዳጅ ያወሩላቸው እንደሆነ ፍሬ ነገሩን
አይጠይቁም:: «ድምፁ እንዴት ነው? የሚወደው ጨዋታ
ምንድነው? ቢራቢሮዎች ይሰበስባል?» አይሉም:: እነሱ
የሚጠይቁት «ስንት ዓመቱ ነው? ስንት ወንድሞች አሉት?
ክብደቱ ስንት ነው?» ብለው ነው:: ያወቁት የሚመስላቸው
ያ ሲሆን ብቻ ነው:: አዋቂዎቹን ሰዎች «ቀለሙ ጽጌረዳ
በመሰለ ጡብ የተሠራ፣ መስኮቱ በቁርዬ አበባ የተጌጠ፣
ጣራው ላይ እርግቦች
የሠፈሩበት ቆንጆ
ቤት አየሁ»
ቢሏቸው ቤቱ
በዓይነ ኅሊናቸው
አይታያቸውም::
«መቶ ሺህ ፍራንክ
የሚያወጣ ቤት አየሁ





ማለት አለብዎት:: ያንጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በአድናቆት፣ «እንዴት ያምር!» ይላሉ::

በተመሳሳይ፣ «ታዳጊው ልዑል ያምራል፣ ይሥቃል በግም ይፈልግ ነበር፣ ይኸ ሁሉ መኖሩን ያስረዳል:: በግ እፈልጋለሁ ካለ የራሱን መኖር አረጋገጠ ማለት ነው» ቢሏቸው፣ በትከሻቸው ምልክት አሳይተው እንደ ሕፃን ያይዎታል! «ልጁ የመጣው ከሕዋ አካል ቢ612 ካሏቸው ግን በጉዳዩ ያምኑበትና እርስዎም ከጥያቄዎቻቸው ይገላገላሉ:: የነሱ ነገር ይኸው ነው:: ቂም መያዝ አያሻም:: አዋቂዎቹን በተመለከተ ልጆች ጠባያቸውን አውቀው መቻል አለባቸው::

እርግጥ፣ እኛ ሕይወትን የተገነዘብነው ግን፣ አኃዞችን እንደ ቀልድ ነው የምናያቸው! ይህንን ታሪክ በተረት መልክ ማቅረብ በወደድኩ ነበር:: እንዴት ቢሉ!

አንድ ጊዜ ከርሱ ትንሽ በምትበልጥ የሕዋ አካል ላይ የሚኖር ወዳጅ ማበጀት የሚፈልግ አንድ ታዳጊ ልዑል ነበር:: የሕይወት ዘይቤ ለሚገባቸው ሰዎች ይህ አቀራረብ እውነት መስሎ በታያቸው ነበር::

ምክንያቱም መጽሐፌን በቀላሉ ቢያነቡት አልወድም:: እነዚህን ትዝታዎቼን ሳወሳ የሚሰማኝ ሐዘን ቀላል አይደለም:: ወዳጄ በጉን ይዞ ከሄደ እነሆ ስድስት ዓመት ሆኗል:: እዚህ በጽሑፍ ላቀርበው የምሞክረው እንዳልረሳው ብዬ ነው:: ወዳጅ ወዳጁን ሲረሳ አሳዛኝ ነገር ነው:: ሰው ሁሉ የልብ ወዳጅ የለውም:: ትኩረታቸውን አኃዞች ላይ ብቻ እንደ ጣሉት አዋቂዎች ልሆን እችላለሁ:: ለዚህም ነው አንድ ሣጥን ቀለምና እርሳሶች የገዛሁት:: ድፍን ዘንዶና ክፍት ዘንዶ ያውም በስድስት ዓመቱ ከመሳሉ በስተቀር ሌላ ምንም ላልሞከረ ሰው አሁን በዚህ ዕድሜው ወደ ሥዕል መመለስ ከባድ ነው! እርግጥ፣ በተቻለ መጠን አብነቱን የሚመስሉ ሥዕሎች ለመሳል እሞክራለሁ:: ይሳካልኛል ብዬ ሙሉ በሙሉ አላምንም:: አንዱ

ንድፍ ይዋጣል፣ ሌላው አልመሰል ይላል። እቁመቱም ላይ ትንሽ እሳሳታለሁ። አሁን እዚህ ላይ ታዳጊው ልዑል በጣም አድጓል። እዚያኛው ላይ በጣም አንሷል። አልብሱም ቀለም ላይ እያመነታሁ ነው። እንደ ነገሩ በዳሰሳ ወዲያ ወዲህ እነካካዋለሁ። በመጨረሻ አንዳንድ ዋና ነጥቦች ላይ መሳሳቴ አይቀርም። ያንን እንግዲህ ይቅርታ ያደርጉልኛል። ወዳጄ ፈጽሞ ማብራሪያ አይሰጥም ነበር። ምናልባት እንደሱ ዓይነት የሆንኩ ይመስለው ይሆናል። የሚያሳዝነው ነገር እኔ እሣጥን ውስጥ ያሉ በጎችን ማየት አይችልም። በመጠኑ እንደ ትልልቆቹ ሰዎች ሳልሆን አልቀርም። ሳላረጅ አልቀርም።

## ፭

በየቀኑ ስለ ሕዋ አካል፣ ስለ በረራ፣ ስለ ጉዞ አንዳንድ ትምህርት አገኝ ነበር። በሐሳቤ መካከል እየመጣ ቀስ በቀስ ነበር የሚገባኝ። እንዲህ እያልኩ ነው በሦስተኛው ቀን የወርካዎችን ፍዳ የደረስኩበት።

አሁንም ይህንን ለማወቅ የቻልኩት በበጉ ምክንያት ነው። ታዳጊው ልዑል ከባድ ጥርጣሬ እንደ ገባው ሰው በድንገት፣

- በጎች በእርግጥ ቁጥቋጦ ይበሉ የለም? ሲል አበክሮ ጠየቀኝ።
- አዎ በእርግጥ ይበላሉ።
- ጎሽ! ደስ አለኝ።

የበጎች ቁጥቋጦ መብላት ለምን ይህን ያህል ቁም ነገር እንደ ተሰጠው ሊገባኝ አልቻለም ነበር። ታዳጊው ልዑል ግን ቀጠል አድርጎ፡

- ስለዚህ ወርካዎችንም ይበላሉ? አለኝ።

ወርካዎች የቤተክርስቲያን ሕንፃ የሚያካክሉ ዛፎች ናቸው እንጂ ቁጥቋጦዎች አለመሆናቸውንና በዚህም ላይ የዝሆን

መንጋ እንኳን ይዞ ቢሄድ መንጋው አንዱን ወርካ በልቶ እንደማይጨርስ ታዳጊውን ልዑል አስረዳሁት።

የዝሆኑ መንጋ ጉዳይ ታዳጊውን ልዑል አሣቀው።

- አንዱን ባንዱ ላይ ማደራረብ ያስፈልግ ይሆናል...።


ግን አስተዋይነት በተሞላ አባባል እንዲህ አለ፣

- ወርካ ከማደጉ በፊት ለጋ ሆኖ ነው የሚጀምረው።

- ልክ ነው! ግን ያንተ በጎች ለጋ ወርካ እንዲበሉ የምትሻው ለምንድነው?

ሲመልስልኝ ልክ እንደማያከራክር ነገር፣ «ታዲያስ! ምን ማለትህ ነው!» አለኝ። እኔም ችግሩን አስቤ ለመገንዘብ ከባድ የአእምሮ ጥረት አስፈለገኝ።

በእርግጥም እታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ በማናቸውም ሕዋ አካላት እንደሚኖረው ጥሩ ሣርና አረም አለ። ስለዚህ ጥሩ ሣር ጥሩ ዘር መጥፎ ሣርም መጥፎ ዘር አለው ማለት ነው። ዘሮቹ ግን በዓይን አይታዩም። አንዷ የቀበጠች ቅንጣት እስክትነቃ ድረስ በከርሰ ምድር ምስጢር ውስጥ ተሠውረው ይኖራሉ። ያቺ ቅንጣት እየተንጠራራች ስትፈራ ስትቸር ውብ የሆነ ሰው የማይነካ ለጋ ቀንበጧን አስቀድማ ወደ ሰማይ ትገፋለች። የፍጅል ወይም የጽጌረዳ ቀንበጥ ከሆነ እንደ ልቡ እንዲበቅል መተው ይቻላል። አረም ከሆነ ግን ዘሩ እንደ ታወቀ ወዲያው መንቀል ያስፈልጋል።



ይህ ሲሆን በታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ በጣም አስቸጋሪ አዝርእት ነበሩ...።



የወርካ አዝርእት ናቸው። የሕዋ አካሉን መሬት ወረውታል። ዋርካ ደግሞ ከዘገዩ ለመገላገል ፈጽሞ አይቻልም። ሕዋ አካሉን በሙሉ ያጣበዋል።

ሥሮቹ ዘልቀው ይሰረስሩታል። ሕዋ አካሉ ካነሰና ዋርካዎቹ ከበዙ ሕዋ አካሉን ያፈነዱታል።
«ታዳጊው መስፍን ቆየት አለና ሥርዓቱን የማክበር ጉዳይ

ነው አለኝ:: ጧት ራስን ካጸዱ በኋላ ሕዋ አካሉንም በጥንቃቄ ማጽዳት ያስፈልጋል:: የወርካ ተክል በቡቃያነቱ ከጽጌረዳ ተክል ጋር በጣም ስለሚመሳሰል ገና ልዩነቱ ሲታወቅ ሥራዬ ብሎ መንቀል ያሻል:: ሥራው እጅግ ያስለቻል እንጂ አያስቸግርም::»

አንዱን ቀን ይህ ነገር አገሬ ልጆች ራስ ውስጥ ደኅና አድርጎ እንዲገባ ጥሩ ሥዕል ተግቼ እንድሠራላቸው መከረኝ:: «መንገድ የተጓዙ ዕለት ሊጠቀማቸው ይችላል አለኝ:: አንዳንድ ጊዜ ሥራን ለነገ ማሳደር አይጐዳም:: ወርካን በተመለከተ ግን ሥራውን ማሳደር ታላቅ አደጋ ነው:: አንድ ሰነፍ ግለሰብ ይኖርበት የነበረ ደሴት አስታውሳለሁ...:: ሦስት ችግኞችን ቸል ብሎ ነበር::»

ታዳጊው ልዑል የነገረኝን እየተከተልሁ ያንን ሕዋ አካል ሣልኩት:: አነጋገሬ እንደ ሥነ ምግባር አስተማሪ እንዲሆን አልፈልግም:: ነገር ግን የዋርካን አደጋ ሰው ስለማያውቀውና አንድ ሕዋ አካል ላይ እግር ጥሎት የሚወድቅ ሰው ሊደርስበት የሚችለው ችግር እጅግ ከባድ ስለሆነ ለአሁን ብቻ ከንግግር መቆጠቤን ትቼ የምናገረው ነገር አለኝ:: «ልጆች! ወርካ ተጠንቀቁ::» ይኸንን ሥዕል ብዙ የደከምኩበት እንደኔ ለረዥም ጊዜ ባለማወቅ ይጋፈጡት ከነበረው አደጋ እንዲጠነቀቁ ነው:: የምሰጠው ትምህርት አስፈላጊ ነው:: «እዚህ እመጽሐፍ ውስጥ ወርካውን የሚያህል ሌላ ትልቅ ሥዕል ለምን አልገባም ትሉ ይሆናል:: መልሱ ቀላል ነው፣ ሞክሬ ስላቃተኝ ነው:: ወርካዎቹንም የሣልኩት የጭንቀቱ ስሜት ገፋፍቶኝ ነው::



ወርካዎች



## ፯

አይ ታዳጊው ልዑል ትካዜ የተሞላ ኑሮህን እንዴት እንደምትገፋው ቀስ እያለ እየገባኝ ነው። ከጀንበር መጥ ለቅ ውበት በስተቀር ሌላ ምንም የሚያዝናናህ ነገር ሳታይ ለረዥም ጊዜ ኖረሃል። ይኽንንም አዲስ ሁኔታ ለማወቅ የቻልኩት በተገናኘን በአራተኛው ቀን ጧት፣

- ጀንበር ስትጠልቅ ማስተዋል ደስ ይለኛል... ስትለኝ ነው።

- ግን መጠበቅ ያስፈልጋል።

- የሚጠበቀው ምንድነው?

- ጀንበር እስክትጠልቅ።

በፊት በጣም እንደ መገረም አልክና ከዚያ መልስህ በራስህ ሣቅህ፣ ቀጥለህም፣

- አሁንም አገሬ ያለሁ ይመስለኛል! አልከኝ።

እርግጥ አሜሪካን አገር እኩለ ቀን ሲሆን እንደሚታወቀው እፈረንሣይ አገር ጀንበር ትጠልቃለች:: ጀንበር ስትጠልቅ ለማየት በአንዲት ደቂቃ እፈረንሣይ አገር መድረስ ብቻ ነው:: የሚያሳዝነው ፈረንሣይ አገር በጣም እሩቅ መሆኑ ነው:: አንተ ግን አነስተኛ የሕዋ አካልህ ላይ ሆነህ ወንበርህን ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ማድረግ ብቻ ነው:: ከዚያ የጀንበሯ መጥ ለቅ እንደ ልብህ ይታይሃል::

- አንድ ቀን አርባ አራት ጊዜ ጀንበር ስትጠልቅ አየሁ!

ትንሽ ቆየህና ንግግርህን በመቀጠል፣

- ታውቃለህ... ሐዘን ሲያጠቃህ ጀንበር ስትጠልቅ ማየት ደስ ይላል...::

- አርባ አራት ጊዜ ያየህ ዕለት በጣም አዝነህ ነበረ ማለት ነው?

ታዳጊው ልዑል መልስ አልሰጠም::

## ፯

በአምስተኛው ቀን አሁንም በበጉ የተነሣ ሌላ የታዳጊው ልዑል የሕይወቱ ምስጢር ተገለጸልኝ:: ለረዥም ጊዜ በዝምታ ሲያወጣ ሲያወርድ የነበረውን ጥያቄ ዱር ዱር ሳይል በድንገት አቀረበልኝ:

- በግ ቁጥቋጦ ከበላ አበባም ይበላል ማለት ነው?

- በግ ያገኘውን ሁሉ ነው የሚበላው::

- እሾሃም አበቦችም ቢሆኑ?

- አዎ:: እሾህ የሚያበቅሉ አበቦችም ቢሆኑ::

- ታዲያ እሾሁ ምን ፋይዳ አለው?

እኔ ምን አውቃለሁ። አንድ በጣም የጠበቀ የሞተር ቡሎን ለመፍታት በመታገል ላይ ነኝ። ብልሽቱ ከባድ እንደ ሆነ እየታየኝ ስጋት ይዞኛል፣ በዚህ ላይ የሚጠጣ ውኃ መቀነስ የባሰ ችግር እንዳያስከትል እየፈራሁ ነው።

- እሾህ የሚጠቅመው ለምንድነው?

ታዳጊው ልዑል አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ እሺ ብሎ አይለቅም ቡሎኑ አበሳጭቶኝ ስለነበረ አፌ እንዳመጣ ስመልስለት፣

- እሾህ የአበባዎች ክፋት ከመሆኑ በስተቀር ሌላ ሚና የለውም።

- ኧረ እባክህ!

- ጸጥ አለና እንደ ተቆጨ ሰው፣

- አላምንህም! አለኝ። አበባዎች ደካሞች ናቸው፣ የዋሆች ናቸው። እንዳቅማቸው ይግደረደራሉ። እሾህ ስላላቸው አስፈሪ የሆኑ ይመስላቸዋል...።

መልስ አልሰጠሁም። ልክ በዚህ ጊዜ ይኸ ብሎን እምቢ ካለ በመዶሻ አፈልሰዋለሁ።

ታዳጊው ልዑል እንደገና ረበሸኝ፣

- አንተ አበቦች ... ይመስልሃል?

- አይ! አይ! አላምንበትም እንደ መጣልኝ መለስኩለት። እኔ አሁን ቁም ነገር ያለው ሥራ እየሠራሁ ነው።

በድንጋጤ አየኝ።

- ቁም ነገር?

መዶሻ ይዤ፣ ጣቶቼን ግራሶ አቆሽሿቸው፣ ለሱ በጣም አስቀያሚ ሆኖ የታየው አንድ ጥቁር ነገር አጐንብሼ ሳጠና ተመለከተኝ።

- አነጋገርህ ነፍስ እንዳወቀ ሰው ነው።

አፈር አልኩ፤ እሱ ግን ምንም ሳይራራልኝ፣

- ትዘባርቃለህ ... ተምታቶብሃል!

በእውነት በጣም ተበሳጭቶ ነበር። ወርቅማ ጉፈሬውን አየር

ላይ አወራጨ:: አንድ ቅላቱ ደም የሚመስል ሰው ያለበት ሕዋ አካል አውቃለሁ:: ያ ሰው አበባ አሽትቶ አያውቅም:: ኮከብ አይቶ አያውቅም:: ሰው ወዶ አያውቅም:: ድምር ከመደርደር በቀር ሌላ ሥራ ሠርቶ አያውቅም:: ቀኑን ሙሉ እንዳንተ፣ «እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ! እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ» እያለ ስለሚውል ልቡ በኩራት ያብጣል:: ግን እንጉዳይ ነው እንጂ ሰው አይደለም::

- ምንድነው ያልከው?
- እንጉዳይ!



ታዳጊው ልዑል በዚህ ጊዜ ፊቱ በቍጣ ከሰል መስሎ ነበር::

- አበቦች እሾህ በማውጣት ሚሊዮን ዓመት አስቈጥረዋል:: ቢሆንም በጎች አበባ ሲበሉ ሚሊዮን ዓመት ሆኗቸዋል:: ምንም ላይጠቅማቸው እሾክ ለማውጣት ይህን ያህል ለምን እንደ ደከሙ ለመገንዘብ መሞከር ዋጋ የለውም:: የበጎችና የአበባዎች ጦርነት ፋይዳ የለውም? ቁም ነገሩና አስፈላጊነቱ አንድ ፊቱ ፍም የሚመስል ወፍራም ሰው ከሚደረድረው ድምር አይበልጥም? ከኔ ሕዋ አካል ውጪ ዓለም ላይ የትም የማይገኘውን ብርቅዬ አበባ በጉ ዝም ብሎ ጧት ተነሥቶ የሚያደርገውን ሳያውቅ ጨርግዶ ቢያወድመው ይኸ ከባድ ጉዳይ አይደለም?



ፊቱ ቀይ ሆነና ወዲያው በመቀጠል፣

- በብዙ ሚሊዮን በሚቈጠሩ ከዋክብት መካከል አንድና ብቸኛ የሆነ አበባ የሚወድ ሰው ደስ እንዲለው ከዋክብቱን ማየት ብቻ ይበቃዋል:: «እነዚያ መካከል አንዱ ላይ የኔ አበባ አለ:: በጉ አበባውን ከበላው ግን ከዋክብቶቹ ሁሉ ጨለሙበት ማለት ነው! ይኸ ከባድ ጉዳይ አይደለም?»

ሌላ ምንም ሊያክልበት አልፈለገም። በድንገት እንባ ተናነቀው። መሽቶ ነበር። እኔ መጫያዎቼን ጥዬ ነበር። መደሻውም ቡሉኑም ውኃ ጥሙም ሞቱም ደንታ አልሰጡኝም። አንድ ኮከብ ላይ እኔ ሕዋ አካል መሬት ላይ አንድ ታዳጊ ልዑል ማጽናናት ነበረብኝ። እቅፍ አድርጌ እሽሩሩ «የምትወደው አበባ ለምንም ዓይነት አደጋ አልተጋለጠም፣... ለበግህ ልባብ እሥልልሃለሁ» አልኩት። ለአበባህም ጥሩር እሥልልሃለሁ... እናም...» የምለው ጠፋኝ። ግራ ገባኝ። እንዴት ልድረስበት፣ እንዴት ልቡን ላግኘው፣... የእንባ ነገር ምስጢሩ ብዙ ነው።

፰

ጊዜ ሳይፈጅብኝ ያንን አበባ በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ ቻልኩ። ታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ ቦታ የማይወስዱና ሰው የማያስቸግሩ በአንድ ዙር ቅንጣቶች የተጌጡ ጥራት ያላቸው አበባዎች ሁልጊዜም ነበሩ። ጧት እመስኩ ላይ ብቅ ይሉና ሲመሽ ጥፍት ይሉ ነበር። ያ ብርቅዬ አበባ ግን የበቀለው ከየት እንደ መጣ ካልታወቀ ዘር ነበርና ያችን ከሌሎቹ የተለየችውን ቡቃያ ታዳጊው ልዑል ከቅርብ ይጠብቃት ነበር። አዲስ የወርካ ዘር ልትሆን ትችላለች። ትንሿ ቁጥቋጦ ግን ወዲያው ማደጉን ተወችውና ለማበብ ትዘጋጅ ጀመር። ታዳጊው ልዑል በጣም ትልቅ የሆነ እምቡጥ ተመቻችቶ ሲቀመጥ እያየ ተአምራዊ ክስተት ይወጣዋል ብሎ ተስፋ ሲያደርግ አበባዋ ግን አረንጓዴ ክፍል ውስጥ ተሸሽጋ መሽሞርሞሯን በረጅሙ ተያያዘችው። ቀለማቱን ስትመርጥ በጥንቃቄ ነበር። ስትለብስ በእርጋታ ቀንበጦቿን የምታስተካክለውም አንድ በአንድ ነበር። ስትፈካ ቀንበጦቿ እንደ ጓኸማ ተጨማደው እንዲወጡ አትፈልግም ውበቷ ሙሉ በሙሉ ሲያንጸባርቅ ከማሳየት በቀር ሌላ ፍላጎት

አልነበራትም። አዎ፣ ይኸውልህ! በጣም ሽቅርቅር ናት። በምስጢር ስትዋብ ብዙ ቀንና ሌሊት ፈጀባት። እናም አንድ ቀን በጧት ልክ ጎሕ በሚቀድበት ሰዓት ብቅ አለች።

ከዚያም በከፍተኛ ጥንቃቄ ትሠራ የነበረችው እያዛጋት፣

«እፎይ! ገና መንቃቴ ነው... ይቅርታዎን... ጸጉሬንም ገና አልተበጠርኩም» አለችው።

ታዳጊው ልዑል አድናቆቱን መቈጣጠር አቃተውና፣

- አቤት ማማርዎ! አላት።

- አይደል? አለችው ቀስ ብላ። የተወለድኩትም ከፀሐይቱ ጋር ነው...።

ታዳጊው ልዑል ትሕትና እንደማያጠቃት በትክክል ግን በጣም ታባባለች!

- ቀበል አደረገችና የቍርስ ሰዓት የደረሰ ይመስለኛል፣ እባክዎ እንዳይረሱኝ...።

ታዳጊው ልዑልም እፍር ብሎ፣

አንድ አትክልት ማጠጫ ሙሉ ጥሩ ውኃ አመጣና አቀረበላት።

በመጠኑም ቢሆን ጥርጣሬ

በሚያይበት ከንቱነቷ ገና ከመነሾው አሠቃይታው ነበር።

ለምሳሌ አንድ ቀን ስለ አራቱ እሾሆቿ ታዳጊውን ልዑል፤

- ነብሮቹ መጥተው እስቲ በጥፍራቸው ይሞክሩኝ! አለችው።





- ታዳጊው ልዑል፣ «እኔ ሕዋ አካል ላይ ነብር የለም፣ ነብር ደግሞ ሣር አይበላም:: ብሎ መለሰላት::

- እሷም በለስላሳ ድምፅ፣ «እኔኮ ሣር አይደለሁም» አለችው::

- ይቅርታዎን ...

- ነብር ምኑም ምኑም አያስፈራኝ፣ እኔ በጣም የምጠላው ተባራሪ ንፋስ ነው:: ከለላ የሚሆነኝ ግርዶሽ የለዎትም? «የተባራሪ ንፋስ ጥላቻ ብሎ ነገር...:: ለአንድ ተክልስ ዕድል ማጣት ነው» አለ ታዳጊው ልዑል:: «ይቺ አበባ ችግር አለባት...»

- ማታ ክዳን ይደፉብኛል፣ አገርዎ በጣም ይበርዳል፣ አቀማመጡ ትክክል አይደለም:: የኔ አገር... ንግግሯን አቋረጠች::

የመጣችው ገና ጥሬ ዘር ሆና ነው:: ስለ ሌላው አገር ምንም ማወቅ ሳትችል ማለት ነው:: እንዲህ ያለ የሞኝ ውሸት ስታውጠነጥን ስለ ደረሰኩባት አፍራ ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ መሳል አለች፣ ታዳጊውን ልዑል ጥፋተኛ ለማድረግ::

- ግርዶሹን እንዴት አደረጉልኝ?

- ላመጣው ነበር ንግግርዎን ይጨርሱ ብዬ ነው::

እንዲጸጽተው ብላ ሳሷን አውቃ አከረረችው:: ይኸ ሲሆን ታዳጊው ልዑል ፍቅሩ ቀና ይሁን እንጂ





አበባይቱ ወዲያው ጥርጣሬ ሳታሳድርበት አልቀረችም። ለፍሬቢስ አነጋገሯ ዋጋ እየሰጠ በጣም አዝኖ ነበር።

«ባልሰማት ይሻለኝ ነበር። አበቦችን ማየትና ማሽተት ነው እንጂ መስማት በፍጹም አያስፈልግም። የኔ አበባ ሕዋዬን በመዓዛዋ ብታውደውም እኔ መደሰቱን አላወቅሁበትም። ስለ ጥፍሮች ያወራችው ወሬ የመሳሳት ስሜት ሊያሳድርብኝ ሲገባው እንዲያውም አበሳጭቶኝ ነበር ...» ብሎ አንድ ቀን ምስጢሩን አካፍሎኛል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የሆዱን አውጥቶ ነገረኝ፤

«ያን ጊዜ ምንም ሊገባኝ አልቻለም እንጂ!እሷን መገመት የነበረብኝ በንግግሯ ሳይሆን በተግባሯ ነበር። በመዓዛዋ እያወደች ብርሃን ትፈነጥቅልኝ ነበር። መኰብለል አልነበረብኝም። ከሞኝ ብልጣ ብልጥነቷ ጀርባ የባሕሪዋን አዛኝነት ማወቅ ነበረብኝ። ያበቦች ጠባይ አቤት የቅራኔው ብዛት! ልጅ ስለ ነበርኩ መውደዱን አላወቅሁበትም።



# ፱

ለመኰብለል በጼር አእዋፍ የፍልሰት በረራ የተጠቀመ ይመስላል:: የጉዞው ዕለት በጧት ተነሥቶ ሕዋውን በሚገባ አስተካከለ:: ያልጠፉትን እሳተ ገሞራዎች ጭስ ማውጫ በጥ ንቃቄ አጸዳ:: ያልጠፉ እሳተ ገሞራዎች ሁለት ነበሩት:: የነሱ መኖር ጧት ጧት ቁርስ ለማሞቅ በጣም ምቹ ነው:: አንድ የጠፋ እሳተ ገሞራም ነበረው:: እሱ እንደሚለው «መቼም አይታወቅና» ያንንም ከንፈሩን ጠራረገው:: መተንፈሻቸው በንጹሕ ከተያዘ እሳተ ገሞራዎች ቀስ እያሉ በሥርዓት ይንበለበላሉ እንጂ አይፈነዱም:: የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንደ ምድጃ እሳት ነው:: በርግጥ እኛ እምንኖርባት ምድራዊት ዓለም ላይ መጠናችን በጣም አነስተኛ ስለሆነ እሳተ ገሞራዎቹን ለማጽዳት ይሳነናል:: ብዙ ችግር የሚያመጡብንም በዚሁ ምክንያት ነው::

ታዳጊው ልዑል ትንሽ እየተከዘ የቀሩትን የወርካ ችግኞች ነቀላቸው:: ተመልሶ መምጣት የሌለበት መስሎት ነው:: ያን ዕለት ጧት ግን የወትሮ ተግባሩን ሁሉ ያከናወነው በጣም ደስ እያለው ነው:: አበባዋን ለመጨረሻ ጊዜ ውኃ አጠጥቶ ክዳኑን ሊያደርግላት ሲል እንባ እንባ እንዳለው ተሰማው::

- ደኅና ሁኚ አላት አበባዋን::
- እሷ ግን አልመለሰችለትም::
- አሁንም ደኅና ሁኚ አላት::
- አበባዋ ሳል አሳላት:: ግን በያዛት ጉንፋን ምክንያት አልነበረም::
- መጨረሻ «ቀብጬ ነበር» አለችው:: «ይቅርታ አድርግልኝ፤ ደስተኛ ለመሆን ሞክር::»

ሳትወቅሰው መቅረቷ ገረመው:: ግራ ገብቶት ክዳኑን ወደ ላይ ገልብጦ እንደ ያዘ ቆሞ ቀረ:: የረጋ ለስላሳነቷ ሊገባው አልቻለም::



ያልጠፉትን እሳተ ገሞራዎች ጭስ ማውጫ
በጥንቃቄ አጸዳ።

- አዎ እወድሃለሁ እኮ አለችው አበባይቱ። ሳታውቀው የቀረኸው በኔ ጥፋት ነው። ግድ የለም አንተም ብትሆን እንደኔ ቀብጠህ ነበር። ይኸን ክዳን ወዲያ በለው። ካሁን ወዲያ አልፈልገውም።

- ነፋሱሳ?

- የያዘኝ ጉንፋን ይኸንን ያህል አይደለም። የሌሊቱ ቀዝቃዛ አየር ለጤናዬ ጥሩ ነው። አበባ አይደለሁም።

- አውሬዎቹሳ?

- ቢራቢሮዎች ምን እንደሚመስሉ ማወቅ ከፈለግሁ አንድ ሁለት ቀምቡርሶች በትእግሥት መቀበል መቻል ይኖርብኛል። ቢራቢሮዎች በጣም ያምራሉ ይባላል። ሌላማ ማ ይጠይቀኛል? አንተም እሩቅ አገር መሄድህ ነው። ትልልቆቹን አራዊት እንደ ሆነ ምንም አልፈራ። ጥፍሮች አሉኝ። እንደ ሞኝ እራት እሾኮቿን አሳየችኝ። ከዚያም፣

- አትንቀርፈፍብኝ ያበሽቃል። እሄዳለሁ ብለሃል። ሂድ ወዲያ። ይኸ ሁሉ ስታለቅስ እንዳላያት ነው። ኩራተኛነቷ ይኸ ነው የማይባል አበባ ነበረች...።

## ፲

ታዳጊው ልዑል የሚገኘው በቁጥር 325፣ 326፣ 327፣ 328፣ 329፣ እና 330 ሕዋ አካላት አካባቢ ነበር። ሥራ እንዳይፈታና ትምህርትም እንዲሆነው ይጐበኛቸው ጀመረ። የመጀመሪያው ሕዋ የንጉሥ መኖሪያ ነበር። ንጉሡ በሙጭልጭላ ለምድ የተጌጠ ቀይ የድሃ ካባ ለብሶ ጌጥ በማይበዛበት ዙፋን ላይ በግርማ ሞገስ ተቀምጧል።

- ንጉሡ ታዳጊውን ልዑል ሲያይ ድምፁን ከፍ አደረገና፣ «ጎሽ! አንድ ዜጋ ተገኘ» አለ።

ታጻጊው ልዑልም፣

- ከዚህ ቀደም ሳያየኝ አሁን እንዴት ሊያውቀኝ ቻለ? ብሎ ገረመው:: ለነገሥታት ዓለም ቀላል ሆና እንደምትታያቸው አያውቅም ነበር:: ለነሱ ሰው ሁሉ ዜጋቸው ነው::

- አንጋሽ በማግኘቱ ተኮራርቶ የነበረው ንጉሥ፣ «እስቲ ቀረብ በል ልይህ» አለው::

ታጻጊው ልዑል የሚቀመጥበት ቦታ ባይኑ ቢፈልግ አጣ፣ በንጉሡ ባለ ሙጭልጭላ ካባ ሕዋው ተጣቦ ነበር:: ቆሞ ቀረና ደከሞት ስለ ነበረ አዛጋው::

- እንጉሥ ፊት ማዛጋት ሥነ ሥርዓት መጣስ ነው:: እንዳይደግምህ፣ አለው ንጉሡ::

- ታጻጊው ልዑል አፍሮ፣ «አቅቶኝ ነው፣ ጉዞዬ ረዥም ስለ ነበረ እንቅልፍ አላገኘሁም... ብሎ መልስ ሰጠ::

- እንደዚህ ከሆነ አዛጋ አለው ንጉሡ:: ሰው ሲያዛጋ ካየሁ ብዙ ዓመት ሆኖኛል:: ሲያዛጉ ማየት ብርቅ ሆኖብኛል:: በል አሁንም አዛጋ:: ትእዛዝ ነው::


- ፍራት ፍራት ይለኛል... አልቻልኩም... አለ ታጻጊው ልዑል ፊቱ ቀይ እየሆነ::

- ነው እንዴ! ነው እንዴ! አለ ንጉሡ:: እንግዲያው አንዳንድ ጊዜ አዛጋ፣ አንዳንድ ጊዜ...::

ትንሽ ያልጉመጉማል፤ የተቀየመም ይመስል ነበር::

ንጉሡ ከሁሉ ይበልጥ የሚፈልገው ሥልጣኑ እንዲከበርለት ነው:: እምቢ ማለትን አይቀበልም:: አምባገነን ንጉሥ ነው:: ነገር ግን ደግ ስለ ነበረ የሚሰጠው ትእዛዝ አግባብ ያለው ነበር:: ንጉሡ እየደጋገመ የሚናገረው አንድ አባባል ነበረው፣ ይኸውም «አንዱን የጦር መሪ የባሕር ወፍ ሁን የሚል ትእዛዝ ሰጥቼው ትእዛዜን ሳይፈጽም ቢቀር እሱ ጥፋት የለበትም:: ጥፋቱ የኔ ነው» የሚል ነው::

- ታጻጊው ልዑል እየፈራ እየቸረ፣ «መቀመጥ ይፈቀድልኛል?» አለ::



- ንጉሡ የባለሙጭልጭላ ካባውን ዘርፍ ሰብሰብ አደረገና በታላቅ ግርማ፣ እንድትቀመጥ አዝዤሃለሁ አለው።

ታዳጊው ልዑል ግን እየተገረመ ነው። ሕዋው በጣም አነስተኛ፣ ንጉሡ የሚነግሡው እምን ላይ ነው?

- ግርማዊ ሆይ አለ ታዳጊው ልዑል… ጥያቄ ሳቀርብልዎ ከይቅርታ ጋራ ነው…።

- ንጉሡ ወዲያው ቀበል አድርጎ እንድትጠይቅ ታዝሃል አለው::

- ግርማዊ ሆይ... የምን ንጉሥ ነዎ?

- የሁሉም አለ ንጉሡ በቀላል አባባል::

- የሁሉም?

- ንጉሡ የተቀመጠበትን ሕዋ፣ ሌሎቹን ሕዋ አካላትና ከዋክብቶቹን በተቆጠበ የእጅ ምልክት አሳየው::

- የዚህ ሁሉ?... አለ ታዳጊው ልዑል::

- የዚህ ሁሉ... ብሎ መለሰለት ንጉሡ::

ይኸ ንጉሥ አንባገነናዊ ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዊም ንጉሥ ነው::

- ከዋክብቱ ይታዘዙልዎታል?

- እንዴ! አለ ንጉሡ:: ወዲያው ነው የሚታዘዙልኝ፣ ሥርዓት አልባነት እኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም::

ይህን የመሰለው ሥልጣን ታዳጊውን ልዑል አድናቆት አሳደረበት:: ይህን ሥልጣን የያዘው እሱ ቢሆን ኖሮ በቀን አርባ አራት ሳይሆን ሰባ ሁለት ብሎም መቶ ወይም ሁለት መቶ ጊዜ ወንበሩን ሳያነቃንቅ ጀንበር ስትጠልቅ ለማየት በቻለም ነበር!

ጥሏት የመጣው ሕዋ ትዝ እያለችው ትንሽ ያዝን ስለ ነበረ እንደምንም ብሎ ተደፋፈረና ንጉሡ አንዲት ነገር እንዲፈቅድለት ጠየቀው፣

- ፀሐይ ስትጠልቅ ማየት እፈልጋለሁ... ደስ እንዲለኝ... ፀሐይቱን እንድትጠልቅ ይዘዟት...::

- አንዱን የጦር መሪ እንደ ቢራቢሮ ከአበባ ወደ አበባ እንዲበርር ወይም አስጨናቂ ተውኔት እንዲጽፍ ወይም ደግሞ ወደ ባሕር ወፍ እንዲለወጥ ትእዛዝ ብሰጠውና የታዘዘውን ሳይፈጽም ቢቀር ከእኔና ከርሱ ጥፋተኛው ማን ሊሆን ነው?

- ታዳጊው ልዑል ቍርጥ አድርጎ፣ እርስዎ ነዎት አለው::

- ትክክል:: ከእያንዳንዱ መጠየቅ የሚገባው ሊሰጥ የሚችለውን ብቻ ነው፣ አለ ንጉሡ ሲመልስለት:: የሥልጣን ዋና መሠረቱ

አግባብነት ነው። ሕዝብህን ባሕር ዘለህ ግባ ብለህ ብታዘው አብዮት ያስነሣል። ትእዛዜን የማስከበር መብት የሚሰጠኝ የትእዛዞቼ ተገቢነት ነው።

አንድ ጊዜ ያቀረበውን ጥያቄ ፈጽሞ የማይዘነጋው ታዳጊ ልዑል፣ «ታዲያ የኔ የፀሐይቱ መጥለቅ ጉዳይ እንዴት ሊሆን ነው?» ብሎ አስታወሰ።

- ፀሐይቱ ትጠልቅልሃለች። አስገድዳታለሁ። ባስተዳደር ጥበቤ ግን ሁኔታው አመቺ እስኪሆን ድረስ እጠብቃለሁ።

- መቼ ነው? ብሎ ጠየቀ ታዳጊው ልዑል።

- እስቲ ! እስቲ ! ወደ... ወደ... ዛሬማ ወደ አንድ ሰዓት ከአርባ ላይ ትጠልቃለች! እንዴት አድርጋ ትእዛዜን እንደምታከብር ቆይ ታያለህ።

ታዳጊው ልዑል አዛጋው። የፀሐይቱ መጥለቅ ስላመለጠው ቅር ብሎታል። በዚህ ላይ ትንሽ እንደ መሰልቸትም ብሎታልና።

- ንጉሡን እዚህ የሚያቆየኝ ምንም ጉዳይ የለኝም። እንግዲህ ተመልሼ ልሂድ አለው።

- አንድ ዜጋ ስላገኘ ተደስቶ የነበረው ንጉሥ አትሂድ ብሎ መለሰለት። አትሂድ  ሚኒስትር አደርግሃለሁ!

- የምን ሚኒስትር?

- የ ... ፍትሕ!

- ተፋራጅ የለም!

- አይታወቅም አለው ንጉሥ። መንግሥቴን ገና ተዘዋውሬ አልጐበኘሁም። ዕድሜ ተጭኖኛል፣ ሠረገላ ለማስገባት ቦታ ይጠበኛል፣ በእግሬ እንዳልሄድ ይደክመኛል።

- አዎ! አለ ታዳጊው ልዑል ከሕዋ አካሉ ባሻገር ያለውን መልሶ ለማየት ጐንበስ አለና፣ አይቼዋለሁኮ። በዚያም በኩል ማንም የለ።...።

- ራስህ በራስህ ትፈርዳለሃ አለው ንጉሡ። በጣም አስቸጋሪ ሙያ ነው። በሰው ከመፍረድ በራስ መፍረድ ይከብዳል። በራስህ

ላይ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ከቻልክ በእውነቱ ብልህ ነህ ማለት ነው።

- እኔ የትም ቢሆን ራሴን በራሴ መፍረድ እችላለሁ። እዚህ መኖር አያስፈልገኝም።

- እስቲ! እስቲ ! አለ ንጉሡ፣ እኔ ሕዋ ውስጥ አንዱ ሥርቻ አንድ አሮጌ ዓይጥ ያለ ይመስለኛል። ሌሊት እሰማዋለሁ ያንን አሮጌ ዓይጥ ልትዳኘው ትችላለህ። አልፎ አልፎ የሞት ፍርድ ልትፈርድበት ትችላለህ። ይኸንን ካደረግህ ሕይወቱ ያንተ ፍርድ ተገዢ ይሆናል ማለት ነው። አንተ ግን ሕይወቱን ለመቆጠብ ሞት በተፈረደበት ቊጥር በምሕረት ታልፈዋለህ። ያለው አንድ እሱ ብቻ ነው።

- እኔ የሞት ፍርድ መወሰን አልወድም፤ መሄዴ ነው አለ ታዳጊው ልዑል።

- አይሆንም አለ ንጉሡ።

ታዳጊው ልዑል ግን ጓዙን አዘጋጅቶ ጨርሶ ስለ ነበረ አዛውንቱን ንጉሥ ማስቀየም ስላልፈለገ እንዲህ አለው፤

- የግርማዊነትዎን ትእዛዝ በትክክል እንዳከብር ከፈቀዱ የሚሰጡኝ ትእዛዝ አግባብ ያለው ይሁን። ለምሳሌ ግርማዊነትዎ በአንድ ደቂቃ ውስጥ እንድሄድ ሊያዙኝ ይችላል። ሁኔታው አመቺ ይመስለኛል...።

- ንጉሡ ምንም ስላልመለሱለት ታዳጊው ልዑል በፊት ትንሽ አመነና ከዚያ እየጨነቀው ጒዞውን ጀመረ።

- ንጉሡ ቶሎ አለና ድምፁን ከፍ አድርጎ መልእክተኛዬ አድርጌሃለሁ አለው።

አባባሉ ልክ ከፍተኛ ሥልጣን እንዳለው ነው።

ታዳጊው ልዑል በልቡ እነዚህ ትልልቅ ሰዎች ይገርማሉ እያለ ጒዞውን ቀጠለ።

# ፲፩

ሁለተኛው የሕዋ አካል ላይ የሚኖረው አንድ ጉረኛ ሰው ነበር።

- ጉረኛው ሰው ታዳጊውን ልዑል ገና ከሩቅ ሲያየው እሰይ! እሰይ! አድናቂ ሊጎበኝ መጣ አለ።



ለጉረኞች ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ አድናቂዎች ናቸው።

- ጤና ይስጥልኝ አለ ታዳጊው ልዑል። ባርኔጣዎ ያሥቃል።

- ሠላም መስጫ ነው፤ ብሎ መለሰለት ጉረኛው። ሆነ ብለው ሲያደንቁኝ እጅ ለመንሣት የማወልቀው ነው። የሚያሳዝነው ነገር በዚህ በኩል ማንም አያልፍም።

- ታዳጊው ልዑል ምንም ስላልገባው «ነው እንዴ?» አለ።

- ውስጥ እጆችህን አማታ ብሎ መከረው ጉረኛው።

- ታዳጊው ልዑል እጆቹን አማታ።



ጐረኛው በትሕትና ባርኔጣውን አውልቆ እጅ ነሣ፡፡

ታዳጊው ልዑል በሆዱ ይኸ ደግሞ ከንጉሡ ጉብኝት የበለጠ አስቂኝ ጉብኝት ነው አለ፡፡ ውስጥ እጆቹን በድጋሚ አማታ፡፡ ጐረኛውም እንደገና ባርኔጣውን እያወለቀ እጅ መንሣት ጀመረ፡፡ ልምምዱ ሲደጋገምበት ጊዜ ታዳጊው ልዑል ጨዋታው በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሰለቸውና፣

- ባርኔጣው እንዲወድቅ ምንድነው የሚደረገው? ብሎ ጠየቀው፡፡

ጐረኛው ግን አላዳመጠውም፡፡ ጐረኞች መቼውንም ቢሆን ጆሮ የሚሰጡት ለምስጋና ብቻ ነው፡፡

- ለመሆኑ በጣም ታደንቀኛለህ? ብሎ ታዳጊውን ልዑል ጠየቀው፡፡

- ማድነቅ ማለት ትርጉሙ ምንድነው?

- ማድነቅ ማለት በዚህ ሕዋ አካል ውስጥ በመልኬ በአለባበሴ በሀብቴና በእውቀቴ ከማንም እንደምበልጥ መቀበል ማለት ነው::

-- ሕዋው ላይኮ ያለኸው አንተ ብቻ ነህ!

- እስቲ አስደስተኝ:: ያም ሆኖ አድንቀኝ::

- ታዳጊው ልዑል በአሉታ መልክ ትከሻውን በመጠኑ ወደ ላይ ከፍ አደረገና «ለመሆኑ አድናቆት ምን ይደርግልሃል?» አለው::

ከዚያም ታዳጊው ልዑል ተነሥቶ ሄደ::

በጉዞ ላይ ሳለ፣ ትልልቆቹ ሰዎች በእውነቱ ነገራቸው ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው እያለ በሆዱ አሰበ::

# ፲፪

የሚቀጥለው ሕዋ አካል ነዋሪ አንድ ጠጪ ሰው ነበር:: ጉብኝቱ በጣም አጭር ቢሆንም ታዳጊው ልዑል ከታላቅ ትካዜ ውስጥ ገባ::

- በባዶ ጠርሙስና በሙሉ ጠርሙስ ክምችት መካከል በዝምታ ቁጭ ብሎ የነበረውን ጠጪ፣ «ምን እያደረግህ ነው?» ብሎ ቢጠይቀው::

- ጠጪው እየደበተው «እጠጣለሁ» ብሎ መለሰለት::

- ለምን ትጠጣለህ? ቢለው፣

- ለመርሳት አለ ጠጪው::

- ገና ሲያየው አዝኖለት የነበረው ታዳጊ ልዑል፣ «ምን ለመርሳት?» ሲል ጥያቄውን ቀጠለ::

- ጠጪው አቀረቀረና፣ «ሐፍረቴን ለመርሳት» ብሎ እውነቱን ነገረው::

- ታዳጊው ልዑል ሊረዳው ስለ ፈለገ «የሚያሳፍርህ ምንድነው?» ብሎ ለማወቅ ሞከረ።
- የመጠጣት ሐፍረት! አለና ከዚያ በኋላ ፈጽሞ ጸጥ አለ።
ታዳጊው ልዑልም ሐሳብ ገብቶት ተነሥቶ ሄደ።
በጉዞው ላይ ትልልቆቹ ሰዎች እውነትም ነገራቸው ሁሉ እጅግ በጣም ግራ የሚያጋባ ነው እያለ በሆዱ አሰበ።

# ፲፫

አራተኛው የሕዋ አካል የነጋዴው ነበር። በሥራ ከመወጠሩ የተነሣ ታዳጊው ልዑል ሲደርስ ቀና ብሎ እንኳን አላየውም።
- ጤና ይስጥልኝ አለው ልዑሉ። ሲጃራዎ ጠፍቷል።
- ሦስት ሲደመር ሁለት ይሆናል አምስት። አምስትና ሰባት አሥራ ሁለት። አሥራ አምስት ሲደመር ሰባት ሃያ ሁለት። በሃያ ሁለት ላይ ስድስት ሲጨመር ሃያ ስምንት። ሲጃራውን መልሶ ለማቀጣጠል ጊዜ የለም። ሃያ ስድስት ሲደመር አምስት ሠላሳ አንድ። ስለዚህ አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ ነው።
- አምስት መቶ ሚሊዮን ምን?
- እንዴ! አሁንም እዚሁ ነህ? አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ... ምን እንደሆነ ጠፉኝ ... ብዙ ሥራ አለኝ! እኔ ፍሬ ባለው ነገር ነው እንጂ እንዳንተ ጊዜዬን በዋዛ ፈዛዛ አላሳልፍም! ሁለት ሲደመር አምስት ይሆናል ሰባት ...
- አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ ቢሞት የማይለቀው ታዳጊ ልዑል አሁንም፣ «አምስት መቶ ሚሊዮን ምን ብሎ» በድጋሚ ጠየቀው።



ነጋዴው ቀና ብሎ፣

- እዚህ ሕዋ አካል ላይ ሃምሳ አራት ዓመት ስኖር ሰው ያስቸገረኝ ሦስት ጊዜ ብቻ ነው። የመጀመሪያው የዛሬ ሃያ ሁለት ዓመት አንድ ከየት እንደ መጣ የማይታወቅ ጥንዚዛ። ጥዝ ጥዝ በሚል አስከፊ ድምፁ ምክንያት አንድ ድምር ላይ አራት ጊዜ ተሳሳትኩ። ሁለተኛው ከአሥራ አንድ ዓመት በፊት የመጣብኝ ቁርጥማት ነው። የአካል እንቅስቃሴ ያንሰኛል። ለመንከራፈፍ

ጊዜ የለኝም። እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ። ሦስተኛው ... ይኸው እንግዲህ! የት ላይ ነበርኩ አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ...

- ሚሊዮን ምን?

ነጋዴው በሰላም ለመገላገል ተስፋ እንደ ሌለው ገባው፣

- አንድ ሚሊዮን አንዳንድ ጊዜ ሰማይ ላይ የሚታዩት እነዚያ ጥቃቅን ነገሮች።

- ዝንቦች?

- የለም የሚያብለጨልጩ ጥቃቅን ነገሮች።

- ንቦች?

- አይደለም። ሰነፎችን ሰመመን የሚያስይዙ ጥቃቅን ወርቃማ ነገሮች። እኔኮ ቀልድ አላውቅም! ለሰመመን ጊዜ የለኝም።

- አሃ! ኮከቦች ማለትህ ነው?

- በትክክል። ኮከቦች።

- አምስት መቶ ሚሊዮን ኮከቦች ምን ያደርጉልሃል?

- አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ። እኔ ዘንድ ቀልድ የለም ጠንቃቃ ነኝ።

- እነዚህ ኮከቦች ምን ያደርጉልሃል?

- እሚያደርጉልኝ?

- እ!

- ምንም። ንብረቶቼ ናቸው።

- ኮከቦች ያንተ ንብረቶች ናቸው?

- አዎ።

- ከዚህ ቀደም ያየሁት ሌላ ንጉሥ እሱም...።

- ነገሥታት ንብረት የላቸውም። እነሱ አልጋ ይዘው መንገሥ ነው። በጣም የተለየ ነገር ነው።

- የከዋክብት ባለንብረት መሆን ምን ያደርግልሃል?

- ሀብታም ለመሆን ይጠቅመኛል።

- ሀብታም መሆንስ ምን ያደርግልሃል?

- ከተገኙ ሌሎች ኮከቦች ለመግዛት።

ታዳጊው ልዑል በልቡ ይኸኛውም ሰውዬ አስተሳሰቡ ከሞላ ጐደል ከሰካራሙ ጋር ተመሳሳይ ነው አለ።

ያም ሆኖ ጥያቄዎቹን በመቀጠል፣

- የከከቦች ባለንብረት ለመሆን እንዴት ነው የሚቻለው?

- ነጋዴው እየተነጫነጨ «የማናቸው?» ብሎ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት።

- ምን አውቄ። የማንም አይደሉ።

- ይኸ ከሆነ የኔ ናቸው፣ ምክንያቱም መጀመሪያ ያሰብኩበት እኔ ነኝ።

- ይበቃል?

- እንዴ! ባለቤት የሌለው አልማዝ ሲገኝ የራስህ ታደርገዋለህ። ባለቤት የሌለው ደሴት ሲገኝ የራስህ ይሆናል። ከሰው ቀድመህ። አንድ ሐሳብ ቢመጣልህ የባለቤትነት ማረጋገጫ ታወጣና የራስህ ግኝት ይሆናል። እኔም የከዋከብቱ ባለንብረት የሆንኩት ከኔ በፊት ማንም አስቦበት ስላልነበረ ነው።

- እውነትህን ነው አለ ታዳጊው ልዑል። ምን ታደርጋቸዋለህ?

- አስተዳድራቸዋለሁ፤ እየደጋገምኩ እቈጥራቸዋለሁ አለ። ነጋዴው አስቸጋሪ ነው። እኔ ግን ቀልድ አላውቅም!

ታዳጊው ልዑል አሁንም ቢሆን ነገሩ አላረካውም።

- እኔ ያንገት ልብስ ካለኝ ጠምጥሜው ለመሄድ እችላለሁ። እኔ አንድ አበባ ቢኖረኝ አበባዬን ቀጥፌ ለመውሰድ እችላለሁ። አንተ ግን ከዋክብቱን መልቀም አትችልም!

- የለም! ግን ባንክ ቤት በወለድ ላስመዘግባቸው እችላለሁ።

- ምን ማለት ነው?

- የከከቦቼን ቍጥር አንድ ብጣሽ ወረቀት ላይ እጽፋለሁ ማለት ነው። ከዚያም ወረቀቱን መሳቢያ ውስጥ እቆልፍበታለሁ።

- በቃ ይኸው ነው?

- በቃ!

- ትንሹ ልዑል በሃሳቡ፣ «ያሥቃል» አለ። በመጠኑ ልብ ይነካል። ግን የምር የሚሆን አይመስልም።

ታዳጊው ልዑል ስለ ቁም ነገር ያለው አስተሳሰብ ከትልልቆቹ ሰዎች አስተሳሰብ እጅግ የተለየ ነው።

- እኔ አለ ታዳጊው ልዑል ንግግሩን በመቀጠል ሁልቀን ውኃ የማጠጣት አበባ አለችኝ። በየሳምንቱ የማጸዳቸው ሦስት እሳተ ገሞራዎች አሉኝ። ሦስት የሆኑት የጠፋውንም ጭምር ስለማጸዳው ነው። ማን ያውቃል። እሳተ ገሞራዎቹም ሆኑ አበባይቱ የኔ ንብረቶች መሆናቸው ይበጃቸዋል። አንተ ግን ኮከቦቹን አትጠቅማቸውም...። ነጋዴው የሚመልሰው ስላጣ አፉን ከፍቶ ቀረ፣ ታዳጊውም ልዑል ጥሎት ሄደ።

በጉዞው ላይ እንዲያው ዝም ብሎ ትልልቆቹ ሰዎች በእ-ውነቱ ይደንቃሉ እያለ በሆዱ ያስብ ነበር።

## ፲፬

እምስተኛው የሕዋ አካል ዕጹብ ድንቅ ነበር። ከሁሉም ያንሳል። ያለው ቦታ አንድ የጐዳና መብራትና አንድ መብራት አብሪ ብቻ የሚያስገባ ነው። እሰማይ ላይ፣ ቤትም ሕዝብም በሌለበት ሕዋ አካል ላይ አንድ መብራትና አንድ አብሪ ለምን እንደሚጠቅሙ ታዳጊው ልዑል ሊገባው አልቻለም። በሐሳቡ ግን፣

- ይኽ ሰው ምናልባት ግራ ተጋብቶ ይሆናል። ነገር ግን ግራቢስነቱ ከንጉሡም ከጉረኛውም ከነጋዴውም ከጠጪውም ያነሰ ነው። ባይሆን እንኳ የሱ ሥራ ትርጉም አለው። መብራቱን ሲለኩስ አንድ ኮከብ ወይም አንድ አበባ እንደ ተወለደ ይቈጠራል። መብራቱን ሲያጠፋም አበባይቱ ወይም ኮከቧ እንቅልፋቸው ይመጣል ማለት ነው። በጣም ደስ የሚል ሥራ ነው። ደስ የሚል ከሆነ ዘንድ በውነቱ ጠቃሚ ነው።

ሕዋ አካሉ ላይ እንዳረፈ መብራት አብሪውን በአክብሮት እጅ ነሣ፣
- ጤና ይስጥልኝ፣ መብራትህን ምነው አሁን አጠፋኸው?
- መመሪያው ምን ያዛል? ብሎ መለሰለት አብሪው:: ሥራዬ መብራቱን ማጥፋት ደኅና አምሽ::
መልሶ አበራው::
- ምነው መልሰህ አበራኸው?
- መመሪያው ያዛል:: ብሎ መለሰ መብራት አብሪው::
- አልገባኝም አለ::
- ገባኝ አልገባኝ ብሎ ነገር የለም:: መመሪያ መመሪያ ነው:: ጤና ይስጥልኝ::
ከዚያም መብራቱን አጠፋው::
ቀጥሎም ባለ ቀይ መሥመር መሐረቡን አውጥቶ የግንባሩን ላብ ጠረገ::
- ይኸ የኔ ሙያ በጣም ከባድ ነው:: ዱሮ ጥሩ ነበር:: ጧት አጥፍቼ ማታ አበራለሁ:: በተረፈ ቀኑን ሙሉ ማረፍ፣ ሲመሽ መተኛት ነበር::
- ከዚያ ወዲህ መመሪያው ተለወጠ?
- መመሪያው አልተለወጠም፣ አለ መብራት አብሪው:: ይኸ ነው የሚያሳዝነው:: ከዓመት ዓመት የሕዋ አካሉ የመሽከርከር ፍጥነት ሲጨምር መመሪያው ግን አልተለወጠም!
- ታዲያ ምን በጀህ? አለ ታዳጊው ልዑል::
- አሁንማ በደቂቃ አንድ ዙር ስትሽከረከር አንዲት ሰከንድ እንኳን ፋታ የለኝም:: በየደቂቃው ማብራት ማጥፋት ብቻ ነው!
- ያሥቃል! አንተ አገር የቀኑ ርዝመት አንድ ደቂቃ ብቻ ነው!
- ምንም አያሥቅ አለ መብራት አብሪው፤ መነጋገር ከጀመ-ርን ይኸው አንድ ወር ሆኖናል::
- አንድ ወር?
- አዎ፣ ሠላሳ ደቂቃ ሠላሳ ቀን! ደህና እደር::
ብሎም መብራቱን መልሶ ለኰሰ::



ይኸ የኔ ሙያ በጣም ከባድ ነው።

ታዳጊው ልዑልም ይኸንን መመሪያውን በጥብቅ አክብሮ የሚኖር መብራት አብሪ አስተዋለና ወደደው:: ድሮ ራሱ ወንበሩን እያንፏቀቀ ለማየት ይፈልገው የነበረው የጀንበር መጥለቅ ትዝ አለው:: ወዳጁን መርዳት ፈለገና፣

- ታውቃለህ... በፈለግህ ጊዜ ማረፍ የሚያስችልህ ዘዴ አውቃለሁ...::

- የት ተገኝቶ! አለ መብራት አብሪው::

ምክንያቱም አንዱ ሰው ታማኝም ሰነፍም ሊሆን ይችላል::

ታዳጊው ልዑል ቀጥሎ፣

- ሕዋው ከማነሱ የተነሣ በሦስት እርምጃ ትዞረዋለህ:: ሁልጊዜ እፀሐይ ላይ ለመሆን ዝግ ብለህ መራመድ ብቻ ነው:: ማረፍ ሲያምርህ መራመድ... በዚህ ዓይነት ቀኑን እንደ ፈቀድህ ታራዝመዋለህ::

- ይኸ የትም አያደርሰኝ፣ አለ መብራት አብሪው:: እኔ በሕይወቴ የምወደው እንቅልፍ ነው::

- ወይ አለመታደል አለው ታዳጊው ልዑል::

ከዚያም መብራቱን አጠፋው::

ታዳጊው ልዑል መንገዱን ወደፊት ሲቀጥል ይኸንን ሰው ንጉሡም ጉረኛውም ጠጪውም ነጋዴውም ይንቁት ይሆናል:: እኔ ግን ሊሥቁበት የማይገባው እሱ ብቻ ይመስለኛል:: ምናልባት እሱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ነገር ስለሚጨነቅ ይሆናል::

እያዘነ እህህ አለና፣

ቢሆንማ ወዳጅ የማደርገው እሱን ብቻ ነበር:: ግን ምን ያደርጋል ያለበት ሕዋ አካል በእውነቱ በጣም ጠባብ ነው:: ለሁለት ሰው አይበቃም:: ...

ታዳጊው ልዑል ደፍሮ ባይገልጸውም በይበልጥ ይከነክነው የነበረው ያ ዕድለኛ ሕዋ አካል በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ጀንበሯ ሺህ አራት መቶ አርባ ጊዜ ስለምትጠልቅ ነው!